# መቅድም

በኢትዮጵያ ሰዎች ዘንድ የሚያስመስግነኝ ነው በማለት ካርሎ ኮሎዲ የተባለው የኢጣሊያ ጸሐፊ የጻፈውን ፒኖኪዮ ተብሎ የተሰየመውን በዓለም የታወቀውን ስመ ጥሩውን ቆንጆውን የኢጣሊያ መጽሐፍ በአማርኛ ለመተርጎም በሙሉ እምነት ተነሣሁ።

ይህ መጽሐፍ ለወጣቶችና ለሕፃናት ብቻ አልተጻፈም። ታላላቆችም በደስታና በሚያጫውት ንባብ ትንሽ ጊዜያቸውን እንዲያሳልፉ በማለትም እንጂ ነው።

ፒኖኪዮ በውነት በሁሉ ቋንቋ የተተረጎመ በዓለም የተደነቀ ስመ ጥሩ መጽሐፍ በመሆኑ ከብዙም ዘመናት ጀምሮ ለዓለም ሕፃናት ሁሉ ደስታና አጫዋች ሁኖ ይኖራል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ይኸነኑ ዓይነት ደስ የሚያሰኝ ንባብ እያነበቡ እንዲጫወቱና ሲጫወቱ ወዲያውም እንዲማሩ ይኸነን መጽሐፍ ማዘጋጀት የሚገባ መሆኑ ተሰማኝ።

ፒኖኪዮ ይልቁንም ልጆችንም የሚያስተምርና የሚመራ መጽሐፍ ነው። ምንም የዛይማኖት ነገር በፍጹም በውስጡ ባይኖር አእምሮ የሚከፍት መጽሐፍ ነው። ይልቁንም ደግሞ ከእውነት የወጣ ልዩ ታሪክ እያወራ አእዋሳትንም ያለ ባሕርያቸው ባሕርያ እየሰጣቸው ለማሣቀና ለማስደነቀ የተመቸ ውብ መጽሐፍ ሆኖ ታገኙታላችሁ። ብዙም ጊዜ ያስቃል፤ ብዙ ጊዜ ያሳዝናል፤ ብዙ ጊዜ የልጆችን ደካማነት ምን ያህል እንደሆነ ያሳያል፤ በዚህም ስጦታው ነገሩን እየገለበጠ እየዘረዘረና እያሳየ ልጆች ሊያደርጉት የሚገባቸውንና ላያደርጉት የማይገባቸውን ከታላቀ ጥፋትም የሚያደርሰውን ወደ በጎ የሚመራውን ከክፉ ጓደኛ መዋል የሚያመጣውን ችግርና ሁኔታ ሁሉ እየለየ በሰፊው ያሳያቸዋል።

ፒኖኪዮ በአማርኛ ወልደ እንጨት ብዬ የተረጎምኩት እንደ ሰው የሚላወስ የሚናገር የሚስቀ የሚያለቅስ ይልቁንም የልጆች ጠባይ ያለው አንድ የእንጨት ምስል ነው። ከብዙ ብዙ ድካምና ታሪክም በኋላ በመጨረሻው ወልደ እንጨት እንደ ሰው ልጅ አጽምና ሥጋ ለብሶ በዚህ ሁሉ ላይ ደህና ሰውነትና የሥራ ወዳድነት ባሕርይ ያደረበት በውኑ ፍጹም ሰው ይሆናል።

ይኸን አከናውኜ ያቀረብኩላችሁን ስመ ጥሩ መጽሐፍ ምንም ሃይማኖት ሳይቃወም እንደ ጨዋታ እያደረገ የሚያስተምር ሙሉ የምክር ቃልና ደስ የሚያሰኝ አእምሮ የሚያነቃ የንባብ መጽሐፍ ስለሆነ አንባቢው ሳይታወቀው ያለ ማቋረጥ እየተማረና እየተመከረ ንባቡን ይከተላል። ይኸውም መጽሐፍ ፍሬ ነገሩን ለተረዳው ሰው መጽሐፍ መሆኑ ቀርቶ የፈቃደኛና የትጉህ መልካምነት ምክር ይመስላል።

ከኔ ጋራ ሁኖ ብዙውን ሥራ ያከናወነልኝን አቶ ጥላሁን ቸርነትን በብዙ አመሰግናለሁ። ደግሞም ጽሐፈቴን አንብበው ከመጽሐፉም መታተም በፊት ቃሉን ያሻሻሉልኝን ምክር የሰጡኝንና ሁሉ አመሰግናለሁ።

# ወልደ እንጨት

## ፩ኛ

### አናጢው አያ ቲማቲሞ እንደ ልጅ የሚያለቅስና የሚስቅ የእንጨት ቁራጭ እንዳገኘ።

- ድሮ አንድ .....
- ድሮ አንድ ..... - ብዬ ስጀምር ትንሽ አንባቢዎች
- ንጉሥ ነበር! - ብለው ይሉኝ ይሆናል።

አይደለም ተሳስታችኋል። ድሮ አንድ ትንሽ የእንጨት ቁራጭ ነበር። ይኸም የእንጨት ቁራጭ ልዩ ቁንጅና አልነበረውም እንዲያውም የማገዶ እንጨት ነበር።

እንደምን እንደሆነ ሳይታወቅ አንድ ቀን ብቻ ይህ እንጨት ከሽማግሌው አናጢ ቤት ተገኘ። ይኸም አናጢ አያ ገብሩ ይባል ነበር። አፍንጫው ዘወትር ቀይ ስለነበረና ብስል ቲማቲምም ስለሚመስል ሰው ሁሉ በዚሁ ስያሜ አያ ቲማቲሞ የሚል የሙገሳ ስም አወጣለት።

አያ ቲማቲሞ ያን የእንጨት ቁራጭ ገና እንዳየ በደስታ ፈነደቀ እጁንም አሸት አሸት እያደረገ በሆዱ እንደዚህ ሲል አጉረመረመ፤

- ይህ እንጨት ልክ በሚያስፈልገኝ ሰዓት ደረሰልኝ። ለአንድ ጠረጴዛ እግር መሥሪያ አረፍሁ!።

ይኸነንም ብሎ ቀርፊቱን ለማንሳትና ለመጥረብ እንጣጥ ብሎ ተነስቶ ፈጥኖ ምሣሩን አነሳ። እስነዝራለሁም ብሎ እንደ ቃጣ አንድ ረቂቅ ድምጽ ሰምቶ ተገርሞ ቆመ። ረቂቃም ድምጽ እየለመነች - በጣም አትጉዳኝ! - አለች። ይኸን ድምጽ ሲሰማ የዋሁ አያ ቲማቲሞ እንደምን ተገርሞ የቀረ ይመስላችሁ ይሆን! ይኸን ድምጽ የመጣበትን ለማወቅ አያ ቲማቲሞ ቤቱን እየተገላመጠ አየ፤ ግን ማንም አልነበረም፤ ከጠረጴዛውም በታች ቢያይ፤ ምንም አልነበረም ፤ ተዘግቶ የሚኖረውን ሣጥን ከፍቶ ቢመለከት ምንም አላየም፤ ጥራጊና ጥራቢ መጋዝም የሚጠራቀምበትን ቀርጫት ቢያይ ማንንም አላገኘም። የሱቁም መዝጊያ ከፍቶ መንገዱን ቢመለከት ሰውም አልነበረ።

- እንግዲያስ - ብሎ ጮኸ።

እየሳቀና ሽበቱን እያከከ - ገባኝ ገባኝ እኔ ቢመስለኝ ነው እንጂ ድምጽስ አልሰማሁም! ወደ ሥራዬ ልመለስ - አለ።

እንደ ገናም ምሣሩን አንስቶ ያንን የእንጨት ጉራጅ በኃይል ቢመታው - አይ አይ አይ! አሳመምኸኝ! - እያለች ያቺው ረቂቅ ድምጽ እያለቀሰች ጮኸች ይኸን ጊዜ አያ ቲማቲሞ እንደነኀበት ጅብ አፉን ከፍቶ በድንጋጤ አልቦት እንደ ጨው ሟሙቶ ፈዞ ይታይ ነበር። መንፈሱም እንደተመለሰ በድንጋጤ እየተንቀጠቀጠና እየተንተባተበ፤

- ከቶ ይኸ ድምጽ ከየት ነው የሚመጣው? ደግሞም በዚህ ስፍራ ማንም ሰው የለ፤ ምናልባትስ ይህ እንጨት እንደ ትንሽ ልጅ ማልቀስ ተምሮ ይሆንን። ይኸም አይመስለኝም እንጨቱም ይኸው እንደ ሌላው እንጨት ሁሉ አንድ ምንቸት ጎመን ሊቀቀልበት ይችላል። ደግሞስ እውስጡ ሰው ተደብቆ ይሆን? የተደበቀም ቢኖር ለሱ ይብላኝ እንጂ እኔ አሁን አሳየዋለሁ - አለ።

ይኸነንም ብሎ ያንን መከረኛ እንጨት አንስቶ ያለ ሐዘን ከቤቱ ግንብ ጋር ይፈጠፍጠው ጀመር። የሚያለቅስ ድምጽም እንዳለ ለመስማት ጆሮውን አንቀቶ ቆሞ ፪ ፫ ፬ ደቂቃ ቢያዳምጥም፤ ምንም ነገር

አልሰማም። ለመሳቀም እየሞከረ ሽበቱን እየነጨ - ገባኝ! ይኸችን ድምጽ እኔ እንደፈለሰምኸዋት ተረዳሁ። ሥራዬን ልጀምር፣ አለ።

ትልቀም ፍራት ስላደረበት ለመበርታት ትንሽ ትንሽ ማንጐራጐር ጀመረ። ምሣሩንም ወደ ጎን አድረጎ መላጊያውን ሊፈልግ ተነሳ።

አሁንም ያች ድምጽ እየሳቀች - ተው ተው አትኮርኩረኝ! - አለች።

በዚያም ጊዜ አያ ቲማቲሞ ሆይ በመብረቅ እንደ ተመታ እመሬት ወደቀ። ሰውነቱም በተመለሰለት ጊዜ እመሬት ላይ መዘርጋቱ ታወቀው። በድንጋጤ መልኩ ስለተለዋወጠ ሁልጊዜ ቀይ የነበረ አፍንጫው ጭራሹን የተጠበሰ ጉበት መሰለ።

## ፪ኛ

### አያ ቲማቲሞ የእንጨቱን ቁራጭ ለወዳጁ ለአባ ዮሴፍ እንዳበረከተውና አባ ዮሴፍም የሚጨፍርና የሚዘል የሚናገር ምስል ሊሠራ እንደወሰደው።

በዚያን ጊዜም በር ተመታ።

አናጢው ከተቀመጠበት መነሳት እንኳን ሳይችል - ግቡ ግቡ አለ።

ቀንጣ ቀንጣ ያለ አባ ዮሴፍ የተባለ ሽማግሌ መዝጊያውን ከፍቶ ዘው አለ። ምንም አባ ዮሴፍ ቢባል ሽበቱ ቢጫ ስለነበር የሚያገኙት ቀልደኞች ልጆች ሁሉ ለማፌዝ አባ ሽሮ አባ ሽሮ እያሉ ይጠሩት ነበር። አባ ዮሴፍም ትንሽ ነገር የሚበቃው ተናዳጅ ግልፍተኛ ነበርና ወየውለት አባ ሽሮ ለሚለው ሰው ወዲያው ግስላ ሆኖ ለገላጋይ ያስቸግር ነበር።

አባ ዮሴፍም ከመግባቱ - እንዴት ነህ አያ ቲማቲሞ፣ ኧረ በዓለም ምን ትፈጥራለህ? - አለ።

- ጉንዳኖችን ማንበብ አስተምራለሁ - ብሎ አያ ቲማቲሞ መለሰለት።
- ይቀናህ።
- ኧረ ምን እግር ጥሎህ ዛሬ እኔ ቤት መጣህ አባ ዮሴፍ?
- እርግጥ እግሬ ነው አንተ ቤት ዛሬ አንድ ነገር እንድለምንህ የጣለኝ።

አናጢው - በርከክ ብሎ - የጠየቅኸውን ካለኝ ልሰጥህ የተሰናዳሁ ነኝ - አለ።

- ዛሬ ጠዋት እራሴ ውስጥ አንድ ሃሳብ ገባ።
- ምን ሃሳብ። እስኪ ንገረኝ።
- እኔው እራሴ በገዛ እጄ የሚጨፍንና የሚዘል አንድ ቆንጆ የእንጨት ምስል ለመሥራት አሰብሁ። ይኸነን ምስል ይዤ ዓለምን በሙሉ እየዞርኩ የእለት እንጀራዬንና አንድ ዋንጫ ጠላ እንዳገኝ እመኛለሁ። ሃሳቤስ ምን ይመስልሃል - ብሎ ጠየቀው።

አባ ዮሴፍ ገና ንግግሩን ከመጨረሱ ያች የምትመጣበት ስፍራ የማይታወቅ ረቂቅ ድምጽ - ጐሽ ጐሽ አባ ሽሮ - እያለች ጮኸች።

አባ ዮሴፍም አባ ሽሮ መባሉን በሰማ ጊዜ እንደ በርበሬ እስኪቀላ ተናዶ ተንጠራርቶ ዓይኑን በአናጢው አፍጥጦ - እቤትህ መጥቼ እንዴት እንደዚህ ትለኛለህ? ብሎ ጮኸበት።

- ምን አልኹ? ምን አጠፋሁ?
- አባ ሽሮ አልኸኝ!
- አላልሁም!
- ታዲያ እኔ ነኝ? አንተ ነህ!
- አይደለሁም!
- አንተ ነህ!
- አይደለሁም!
- አንተ ነህ አንተ ነህ!

ነገሩ እየተጋጋለ ሰለሔደ ተናነቁ ተደባደቡ ተሰዳደቡም ከአምባጓሮውም በኋላ አያ ቲማቲሞ አባ ዮሴፍን እንደ ቀብ የደፋው የውሸት ሽበት በእጁ መኖሩን አየ፤ አባ ዮሴፍም የአያ ቲማቲሞን የውሸት ሽበት በጥርሱ እንደነከሰ፤

- አያ ቲማቲሞ ሽበቴን መልስ - እያለ ተነፋነፈ
- አንተም የኔን ተፋ! - ብሎ አያ ቲማቲሞ ሽበቱን ከአባ ዮሴፍ ከተቀበለ በኋላ እጅ ለእጅ
ተጨባብጠው ህይወታቸውን ሙሉ መልካም ወዳጆች ሁነው እንዲኖሩ ተማማሉ።
ሰላምም ከሆነ በኋላ - አናጢው - አባ ዮሴፍ ሽረ ምን ኑሯል የምትፈልገው - አለ።
- ምስሉን የምሠራበት ትንሽ እንጨት እፈልግ ነበር። ተሰጠኛለህ?

አያ ቲምቲሞ ደስ ብሎት ያን ዘወትር የሚያስደነግጠውን የእንጨት ቁራጭ ከጠረጴዛ አንስቶ ለሽማግሌው ሊሰጥ ሲቀርብ እንጨቱ ተንፈራግጦ እንደ አሳማ እተድበለበለው አባ ዮሴፍ ጭን ላይ ወደቀ።

- አዬ ያንተ ነገር! ለሰው እቃ ስትሰጥ በእንደዚህ ያለ ትሕትና ነው የምትሰጠው? ሰነከልከኝ እኮ!
- እኔ አይደለሁም እምላለሁ!
- ታዲያ እኔ ነኝ!
- ጥፋቱ ሁሉ የዚህ እንጨት ነው።
- ጥፋቱ የእንጨቱ መሆኑን አውቃለሁ ነገር ግን እግሬ ላይ የወረወርኸው አንተ ነህ!
- እኔ አልወረወርኩብህም!
- ውሸታም!
- አባ ዮሴፍ ተው አትስደበኝ! አለዚያ አባ ሽሮ እልሃለው!
- አህያ!
- አባ ሽሮ!
- ውሻ!
- አባ ሽሮ!
- ቂል ዝንጀሮ!
- አባ ሽሮ!

አባ ዮሴፍም ሶስተኛ ጊዜ አባ ሽሮ በተባለ ጊዜ ዓይኑ በንዴት ጨለመ አናጢው ላይ ተንጠልጥሎ ተናንቀው ተደባደቡ።

ከትግሉ በኋላ አያ ቲማቲሞ አፍንጫው ላይ ተቧጦ ሁለት ቦታ ሲደማ አገኘው። አባ ዮሴፍም ከኮቱ ሁለት አዝራር ጎድሎበት አገኘው።


ከዚህ ሁሉ በኋላ እጅ ለእጅ ተጨባብጠው እስከ ጊዜ ሞታቸው መልካም ወዳጆች ሁነው እንዲኖሩ ተማማሉ።

ብሎም አባ ዮሴፍ ያን እንጨት ቁራጭ አንስቶ አያ ቲማቲሞን አመስግኖ እያነከሰ ወደ ቤቱ ሄደ።

## ፫ኛ

*አባ ዮሴፍ ወደ ቤቱ ተመለሶ ምስሉንም ሠርቶ ወልደ እንጨት ብሎ ስም እንዳወጣለትና የወልደ እንጨትም የመጀመሪያ ኩታራነት።*

የአባ ዮሴፍ ቤት ትንሽ የደሃ ጎጆ ሆና በጭራሮ የምትዘጋና ኖራ የተቀባች ነበረች። የቤት እቃውም እንደአቀሙ አንድ መናኛ አልጋ አንድ አንካሳ ብርጩማ አንድ የተሰነካከለ ጠረጴዛ ነበሩት። እውስጡም ግድግዳ ላይ እሳት ይታይ ነበር ነገር ግን እሳቱ ስዕል ነበር ደግሞም ከእሳቱ በላይ የሚንተከተክና የሚፈላ የሚጨስ የሚመስል ማሰሮ ተስሎ ስለነበር የሚታየው ጭስ የውነት ጭስ ይመስል ነበር።



አባ ዮሴፍ ወልደ እንጨትን እንደ ሠራ

እቤቱ እንደገባ አባ ዮሴፍ ወዲያው የአናጢ መሣርያውን ሰብስቦ ምስሉን መቅረፅና መሳል ጀመረ።

- ምን ስም ባወጣለት ይሻል ይሆን - እያለ ከአለመ በኋላ ወልደ እንጨት እለዋለሁ ፤ ይኸም ስም እድላም ያደርገዋል፤ የወልደ እንጨት ዘር የተባሉትንም ሁሉንም አውቃቸዋለሁ። ብዙዎቹ ዕድሚያቸውም እንደምንም አሳልፈዋል፤ ከነሱም ኃብታሙ ምጹዋት ይለምን ነበር - ብሎ ለምስሉ ስም ካገኘለት በኋላ አባ ዮሴፍ ሥራውን ጀምሮ ጠጉር ግንባር ዓይን በቶሎ ሠራ።

ዓይን ከሠራ በኋላ ያ ዓይን ትኩር ብሎ ሲመለከተውና መላወሱንም ባየ ጊዜ ይህ ሽማግሌ ምን ያህል የተገረመና የተደነቀ ይመስላችኋል?።

አባ ዮሴፍ የሚመለከተው ዓይን ባየ ጊዜ በመደነቅና በመሸበር ተናዶም፣ አንተ ክፉ የእንጨት ዓይን ለምን ታየኛለህ? - ሲል ጮኸ። ነገር ግን ምንም መልስ አላገኘም።

ከዚህ በኋላ አፍንጫ ሠራ ያም አፍንጫ ገና እንደተሠራ ማደግ ጀመረ። አድጎ አድጎ አድጎም የማይበቃው ሆነ። የዋሁ አባ ዮሴፍም መከርከሙ አሰለቸው፣ በከረከመው ቁጥር ያ አፍንጫ ይብሱን ያድግ ነበር።

አፍንጫውን ትቶ አፉን ሠራለት። አፉም ተሠርቶ ሳያልቅ በሠሪው ይስቀበትና ያላግጥበት ጀመረ። አባ ዮሴፍ ተናዶ - አትሳቀ - አለው፣ ይኸም ለአለት ድንጋይ የመናገር ያህል ሆነ። እንደገናም - አትሳቅ ነው የምልህ! - ብሎ በዛቻ ቃል ሽማግሌው ቢጮኽ አፉ መሳቁን ትቶ ያለ የሌለ ምላሱን ጉለጎለው።

አባ ዮሴፍ ግን እያየ ያላየ መስሎ ዝም ብሎ ሥራውን ቀጠለ። አሁን ከሠራው በኋላ አገጩን አንገቱን ትከሻውን ሆዱን ክንዱንም እጁንም ሠራለት። እጁንም ሠርቶ ሲጨርስ አባ ዮሴፍ እንደ ቆብ የደፋው የውሸት ሽበት ከራሱ ላይ ሲኼድ ተሰማው ቀና ብሎ ቢያይ ምን ያየ መሰላችሁ? ቢጫ ሽበቱን አምስሉ አወልደ አንጨት እጅ አየ።

- ወልደ እንጨት ሽበቴን ተሎ መልስ! - ብሎ ጮኸ።

ወልደ እንጨትም ሽበቱን እንደመመለስ ከራሱ አጥልቆ እስኪታፈን ድረስ ተከናነበበት። የሠራው ምሥል አላጋጭና አሳቂ መሆኑን ባየ ጊዜ አባ ዮሴፍ ተናዶ አዝኖ፣

- አልማጭ ልጅ ገና ተሠርተህ ሳታበቃ አባትህን ታሳዝናለህ? ክብር ትነሳለህ? ልጄ ደግ አይደለም! ደግ አይደለም! - ብሎ አምባውን አበሰ።

ይሁን እንጂ የቀረው ሥራ እግርና ቀልጥም ብቻ ነበር። አባ ዮሴፍም እግሩን ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ የሠራው እግር አፍንጫውን ረገጠው። በዚህም ይብሱኑ አዝኖ - ይበለኝ ይገባኛል! ይገባኛል አስቀድሞ ማሰብ ነበረብኝ አሁን ግን የሆነ ሆኗልና ምን ይደረግ! - አለ።

ከዚህም በኋላ ወልደ እንጨትን በክንዱ ደገፎ መራመድ ሊያስተምረው እመሬት አሳረፈው። ወልደ እንጨት እግሮቹን ስለደነዘዘውና ገናም መራመድ ስለማያውቅ አባ ዮሴፍ እጆቹን ይዞ ዳዴ ያሰኘው ጀመር።

ድንዛዜው ካለፈለት በኋላ ወልደ እንጨት ብቻውን በቤት ውስጥ በመሄድና መሮጥ ጀመረ በመጨረሻው ግን ከቤት ሹልክ ብሎ ወጥቶ መንገዱን ይዞ ተፈተለከ።

አልማጩም ወልደ እንጨት እንደ ጥንቸል እየተፈናጠረ ስለሸሸና በዚያ በለስላሳ መንገድ እንደ አምሳ ፈረሰኛ መሬቱን እያንጓጓ ስለበረረ አባ ዮሴፍ ሊደርስበት አልቻለም፣ ያዘው! ያዘው! - እያለ እየጮኸ በሩቀ ይከተል ነበር። በመንገድ የነበሩ ሰዎች ግን ይኸነን የእንጨት ምስል እንደ ሚዳቋ ሲበር ሲያዩት ተገርመው ቀመው በኹኔታው ልባቸው እስኪፈርስ ይስቁ ነበር።

*የእድሉ ክፋት በመጨረሻው ወልደ እንጨትን አንድ ዘበኛ አጋጠመው። ይኸም ዘበኛ የሰውን ልፍለፋ ሰምቶ ከጌታዋ ያመለጠች ውርንጭላ ያለች መስሎት ከመንገዱ መካከል እግሩን አንፈራጦ ጉዳት እንዳይመጣ ለማገድና ለመያዝ ተሰናድቶ ቆመ።*

*ወልደ እንጨት ግን እየሮጠ መጥቶ ገና በሩቁ ዘበኛውን ሲያይ መውጫ ብልሃት ይፈልግ ጀመረ። በዘበኛው እግሮች ውስጥ መሹለክን መርጦ ሊሾልክ ሮጠ። ዘበኛውም ያለ አንዳች ችግር አፍንጫውን አሳምሮ ይዞ አቆመው (የምስሉም አፍንጫ ከልክ አልፎ የተሠራው ዘበኛው መያዝ እንዲመቸው ሆነ ተብሎ የተደረገ ይመስል ነበር) በገዛ እጁም አንጠልጥሎ ዘበኛው ወልደ እንጨተን ላባ ዮሴፍ አስረከበው ሽማግሌው ተቀብሎ የምስሉን ጆሮ ለመቆንጠጥ ቸኮለ። ጆሮውንም ለመያዝ ፈልጎ ባጣ ጊዜ እንደምን የተደነቀ ይመስላችኋል? ለምንድነውስ ብትሉ በችኮላና በንዴት ሲሠራው ሳለ ጆሮውን ሰለዘነጋው ነው። ጆሮውንም ስላላገኘ የምስሉን ማጅራት ይዞ ወደ ቤቱ እየነዳና እያርገፈገፈ በዛቻ እንደዚህ አለው፤*

*- በል ወደ ቤታችን እንሂድ። ከቤታችን ከደረስን በኋላ የሚገባህን አሳይሃለሁ።*

*ወልደ እንጨትም አባ ዮሴፍ ስለዛተበት አመሬት ተዘርግቶ አልሄድም አለ።*

*በዚህን ጊዜ ወሬኛ ማቲዎች ዙሪያውን መቆም ጀመሩ። ከማቲዎቹ አንዱ አንድ ሲናገር ሌላው አንድ ነገር ይመልስ ነበር። አንዳንዶቹም፤*

*- ይህ መከረኛ ምስል እውነት አለው፤ አንድ ጊዜ እቤቱ ከደረሰ ይህ ክፉ አባ ዮሴፍ እንደምን እንደሚያደርገው ማን ያውቃል - ሲሉ አኩሌቶቹ፤ - አባ ዮሴፍን ላላወቀው ሰው ደኅና ሰው ይመስላል በልጆች ላይ ግን ግፈኛ ነው፤ - እያሉ ያሽሟጥጡ ነበር። ሌሎቹ ደግሞ፤ - ይኸ ምስል እጁ ቢገባ ሊበታትነው አይመስልም - ይሉ ነበር።*

*አንዱ አንድ ሲል አንዱ አንድ ሲል በመጨረሻ ዘበኛው ወልደ እንጨትን ነጻ ለቀ የዋሁን አባ ዮሴፍን ወደ ወህኒ እያዳፋ ወሰደው። ሽማግሌውም ያልታሰበ ነገር ስላገኘው የሚያደርገውን አጥቶ እንደ ትንሽ ልጅ እያለቀሰና እየተንሰቀሰቀ፤*

*- አልማጭ ከቶ ለዚህ ኖራል ያንን ያህል ስሠራው የደከምሁት? ሲያንሰኝ ነው፤ ይገባኛል! አስቀድሜ ማሰብ ነበረብኝ! - እያለ ወደ ወህኒ ቤት ኼደ።*

*ከዚህ በኋላ የደረሰው የማይመስል ታሪክ ነውና ቀጥሎ እንደተጻፈው አጫውታችኋለሁ።*